# በአማራ ክልል የተከሰተው ግጭት ሰላማዊ መፍትሄ እንዲያገኝ

## የኢትዮጵያ ሴቶች ማህበራት ቅንጅትና አባላቱ ፤ የኢትዮጵያ ሴቶች ለሰላም ግንባታ አባላት እና "የጀንደር ኢን ፎከስ አባላት" (Gender in Focus) የተሰጠ

## ጋዜጣዊ መግለጫ

**ነሃሴ 6/2015 ዓ.ም**

በሴቶች መብቶች ላይ የሚሠሩ ሲቪክ ተቋማት የውይይትና የትብብር መድረክ የሆነው 'ጀንደር ኢን ፎከስ' (Gender in Focus) አባላት፣ የ 35 ሴቶች ማኅበራት ስብስብ የሆነው የኢትዮጵያ ሴቶች ማኅበራት ቅንጅት (ኢሴማቅ)እና የኢትዮጵያ ሴቶች ለሰላም ግንባታ ከሰሞኑ በአማራ ክልል የተከሰተውን ግጭትና አለመረጋጋት በሰላማዊ መንገድ መፍትሄ እንዲያገኝ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

ማንኛውም ግጭት በሰብዓዊ ፍጥረት በተለይም በሴቶችና ሕፃናት ላይ የተለየ ጉዳት እንደሚያስከትል በመገንዘብና እንዲሁም ከዚህ ቀደም በትግራይ ከተከሰተዉ ጦርነት እና ችግር በመማር ነገሮች ሳይባባሱ በሰላማዊ መንገድ ሊፈታ እንደሚገባ አባላቱ ጥሪውን ያቀርባል: ፡

ኢሴማቅ ፤ የኢትዮጲያ ሴቶች ለሰላም ግንባታና የጀንደር ኢን ፎከስ አባላቶች በተለያዩ ግዜያት የሰላም እጦት እና እንግልት እንዲቆም፤ ሰላም እንዲሰፍን በአጠቃላይ የዜጎችን መብት በማሳሰብ ረገድ በርካታ ስራዎችን ሰርተዋል። ይህንንም አስመልክቶ የችግሮቹን ግዝፈት ለማሳየት የተለያዩ የአቋም መግለጫዎች በማዘጋጀትና ለባለ ድርሻ አካላት በማቅረብ የሴቶች እና ህፃናትን ችግር እንዲሰማና የሚደርስባቸው ጉዳት እንዲቆም የበኩላቸውን ጥረት ሲያደርጉም ቆይተዋል።

በተጨማሪም ለተጎዱ ወገኖች አስፈላጊውን ቁሳቁስ በማሰባሰብ እና በየአካባቢው በማቅረብ ረገድ ኢሴማቅ እና አባላቱ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ አድርገዋል።

አሁንም ይህ የተከሰተው ግጭት እንዲቆምና ሰላም እንዲሰፍን የኢትዮጵያ ሴቶች ለሰላም ግንባታ፤ ኢሴማቅ እና 'የጀንደር ኢን ፎከስ' አባላት ከዚህ ቀደም የተለያዩ ጥረቶችን እንዳደረግነው ሁሉ፣ ግጭቶች በሰላም እንዲጠናቀቁ የበኩላችንን ጥረት ማድረጋችንን የምንቀጥል መሆኑን ስማችን ከታች የተገለፀው የዚህ መድረክ አባላት በአንድ ድምፅ እንገልፃለን።

- የኢትዮጵያ ሴቶች ለሰላም ግንባታ
- የኢትዮጵያ ሴቶች ማህበራት ቅንጅት
- አዲስ አበባ ሴቶች ማህበር
- የኢትዮጵያ የሴቶች መብት ተሟጋች
- የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ተሟጋቾች
- ሲቄ የሴቶች ልማት ድርጅት
- ታርካንፊ ለዘላቂ ልማት
- ሳራ ፍትህ ከሁሉም የሴቶች ማኅበር
- ሴቶች ይችላሉ ማህበር
- የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ሴቶች ብሄራዊ ማህበር
- ቃል የተቀናጀ የማህበረሰብ ልማት ድርጅት
- ስብስብ ለሰብዓዊ መብቶች በኢትዮጵያ
- ሲኤስቲ ኢትዮጵያ
- ሃገር አቀፍ ሴት ወጣቶች በጎ አድራጎት ድርጅት
- ሴታዊት ንቅናቄ
- ትምራን
- ሙጀጀጓ ሎካ የሴቶች ልማት ማኅበር-ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል
- የአማራ ክልል ሴቶች ማኅበር
- ቁማን ውሜን ዴቨሎፕመንት አሶሴሽን-ሶማሌ ክልል
- የኢትዮጵያ የሕግ ባለሞያ ሴቶች ማኅበር
- የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ሴቶች ማኅበር

**ነሃሴ 6, ቀን 2015 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ: ኢትዮጲያ**